
ራይድ ኦን ፍሌክስ **(Ride On Flex)** የመጀመሪያው በጥሪ የሚሰራ የህዝብ ትራንዚት አገልግሎት ሲሆን በተመረጡ ግሌንሞንት/ ዊተን (Glenmont/Wheaton) እና ራክቪል (Rockville) ውስጥ ባሉ ዞኖች ውስጥ አገልግሎት ይሰጣል። ይህ አገልግሎት አገልግሎቱን የሚጠቀሙ ሰዎች ራይድ ኦን ፍሌክስ (Ride On Flex) መተግበሪያን(app) በመጠቀም የመጓጓዣ አገልግሎት መጠየቅ ይችላሉ እናም ተጓዦችን ከትራንዚት ማእከሎች፣ የንግድ ማእከሎች፣ የመንግስት አገልግሎት እና ቤቶቻቸው ጋር በሚያገናኙ የፍሌክስ (Flex) ዞኖች ውስጥ ያደርሷቸዋል። ራይድ ኦን ፍሌክስ (Ride On Flex ) ውስን የሆነ መቆሚያ ስፍራ ወይም ውስን የሆነ የስራ መርሀግብር የለውም – የዛኑ ቀን ቀጠሮ ተሽከርካሪ በማይበዛበት ጊዜ ሲያስይዙ ይመጣል፣ ተለዋዋጭ የሆነ አማራጭ ከተለመደው የአውቶብስ የጉዞ መስመር ይልቅ ያቀርባል፣ $1 ራይድ ኦን (Ride On )ክፍያም ያስከፍላል። የፍሌክስ (Flex) አውቶብሶች ዊልቸሮችን ማስተናገድ ይችላሉ እንዲሁም ነጻ ዋይፋይ (WiFi) አላቸው። በግሌሞንት/ዊተን (Glenmont/Wheaton) እና ሮክቪል (Rockville) ዞኖች ውስጥ ትራንስፖርት ለማግኘት የራይድ ኦን ፍሌክስ (Ride On Flex) መተግበሪያን(app) ያውርዱ ወይም ከሰኞ እስከ አርብ ከ6 ኤኤም እስከ 7 ፒኤም ባለው ጊዜ፣ በ 240-301-3842 በመደወል መጓጓዣ ይጥሩ።

ራይድ ኦን ፍላሽ **(Ride On Flash)** የካውንቲው ፈጣን የአውቶብስ ትራንዚት (Bus Rapid Transit, RBT) አገልግሎት ሲሆን ፈጥነት እና ድግግሞሽ ያለው አገልግሎት በአገልግሎት መንገድ 29 ኮሪደር ላይ በሲልቨር ስፕሪንግ እና በርተስቪል መካከል ለመስጠት የተሰራ ነው። ፍላሽ (Flash) አውቶብሶች ልዩ የሆነ አገልግሎት ከአንድ በላይ የሆኑ የመግቢያ በሮች እና መሳፈሪያን ደረጃን በቀላሉ ለመድረስ የሚያስችል፣ እንዲሁም ከመሳፈርዎ በፊት ለመክፈል የሚያስችል የክፍያ ሲስተም ያለው ሲሆን ይህም ተሳፋሪዎችን ከመሳፈራቸው በፊት ፍላሽ (Flash) ጣቢያዎች ላይ በስማርትትሪፕ (SmarTrip) ካርድ፣ በስማርትትሪፕ (SmarTrip) መተግበሪያ(app)፣ ወይም ቲኬት በመግዛት ክፍያ መፈጸም ያስችላቸዋል። ለአውቶብስ ብቻ በሆኑ መንገዶች፣ የትራንዚት ምልክት ቅድሚያ፣ WiFi እና የብስክሌት መስቀያ ያለው የራይድ ኦን ፍላሽ (Ride On Flash) ለፍጥነት እና ውጤታማነት የተዘጋጀ ነው። ተጨማሪ የፍላሽ (FLASH) አገልግሎት ለሌሎች ዋና ኮሪደሮች አገልግሎት መስጠት እንዲችል ወደፊት ታቅዷል።

## ዛሬኑ ከእኛ ጋር ይጓዙ!
## RideOnBus.com




## Fares

| መግለጫ | ክፍያ |
|---|---|
| የተለመደ ክፍያ፣ ቶከን (Token)፣ ወይም ስማርትሪፕ (SmarTrip®) | $1.00 |
| የስማርትሪፕ (SmarTrip®) በመጠቀም ከሜትሮባስ (Ride On) ወደ ራይድ ኦን (Metrobus) ዝውውር | $1.25 |
| ከሜትሮ ሬል (Metrorail) ወደ ራይዳኦን (Ride On) በባስ ዝውውር | $1.00 |
| ራይድ ኦን (Ride On) ወርሀዊ ፓስ | $22.50 |
| እድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ የሆኑ አረጋውያን በሁሉም መንገዶች የአረጋውያን SmarTrip ካርድን በመጠቀም፣ ትክክለኛ የሆነ የአረጋውያን መታወቂያ ካርድ እና ፎቶ ያለው መታወቂያ ካላቸው በነጻ ይጓዛሉ | ነጻ |
| የሜትሮ አካል ጉዳተኛ ካርድ ያለው አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው በሁሉም መንገዶች ላይ በነጻ መሄድ ይችላል<br>አስተናጋጆች(attendant) በነጻ በሁሉም መንገዶች ላይ ይሄዳሉ | ነጻ |
| መታወቂያ ያለው የሜትሮ አክሰስ (MetroAccess) ሰርትፋይድ ደንበኛ | ነጻ |
| ልጆች በሁሉም መንገዶች ላይ የወጣቶች ክሩዘር ስማርትሪፕ (SmarTrip) ካርድን በመጠቀም በነጻ መሄድ ይችላሉ | ነጻ |
| ኤምቲኤ (MTA) & ኤምኤአርሲ (MARC) ሳምንታዊ እና ወርሀዊ አውቶብስ እና ባቡር ማለፊያዎች እና የትራንዚት ሊንክ ካርዶች (Transit Link Cards, TLC) | ነጻ |
| እድሜያቸው ከ5 በታች የሆኑ ልጆች | ነጻ |
| የስማርትሪፕ በመጠቀም ከራይድ ኦን ወደ ራይድ ኦን አውቶብስ ዝውውር | ነጻ |
| ሜትሮ ባስ (Metrobus) ወደ ራይድ ኦን (Ride On) አውቶብስ ዝውውር | ነጻ |
| ቫንጎ ሾትል (VanGo Shuttle) - Route 28 - ዳውን ታውን ሲልቨር ስፕሪንግ (Downtown Silver Spring) | ነጻ |
| ቤተዝዳ ሰርኩሌተር (Bethesda Circulator) | ነጻ |

በጃንዋሪ 2025 የተሻሻለ

# የራይድ ኦን (Ride On) የተጠቃሚ መመሪያ




## ከእኛ ጋር ይገናኙ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራንስፖርት ዲፓርትመንት

ስልክ፦ 240-777-0311 • 311

101 Monroe St • 5th Floor
Rockville, Maryland 20850

RideOnBus.com

@RideOnMCT

## ይመዝገቡ

የኢሜይል ማሳወቂያዎችን ለማግኘት፦ MontgomeryCountyMD.gov/govdelivery


የአጭር ጽሁፍ መልእክት ማሳወቂያዎችን ለማግኘት፦ MONTGOMERY RIDEON ብለው አጭር ጽሁፍ መልእክት ወደ 468311 ይላኩ

MCDOT

Ride On
Montgomery County Transit

ራይድ ኦን **(Ride On)** በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ምቹ፣ ደህንነቱ አስተማማኝ እና ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ እና ሙሉውን ካውንቲ የሚሸፍን፣ ቅዳሜ እና እሁድን እና በአላትን ጨምሮ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሠጥ ዋነኛ የህዝብ የአውቶብስ አገልግሎት ነው:: የትራንዚት አገልግሎት ክፍል በካውንቲው ራይድ ኦን (Ride On) የአውቶብስ ሲስተም ውስጥ በካውንቲው ባለቤትነት ስር ያሉ 385 አውቶብሶችን በተመለከት እቅድ እና መርሀግብር ያወጣል እንዲሁም ያስተዳድራል፤ በአመት ውስጥ ከ 18 ሚሊዮን በላይ ጉዞዎችን ያደርጋል። የራይድ ኦን (Ride On) ሲስተም ካውንቲው ውስጥ ያሉ ሌሎች የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ከሚሰጡት አገልግሎቶች ጋር በመሆን ለማኅልበት እንዲሆን ተደርጎ የታቀደ ነው።
ከ 80 በላይ በሚሆኑ የጉዞ መስመሮች(routes)፣ ራይድ ኦን (Ride On) እንደ የሜትሮ ጣቢያዎች፣ የገበያ ማእከሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የንግድ ማእከሎች፣ የጤና ማእከሎች እና ተጨማሪ አስፈላጊ መዳረሻዎችን ያዳርሳል። በተጨማሪም ራይድ ኦን (Ride On) ለአውቶብስ ጉዞ የሚያስከፍለው 1 ዶላር ሲሆን፤ ለመጠቀም ቀላል የሆነ፣ የባሶችን ሰዓት ክትትል ማድረግ የሚቻልበት የስልክ መተግበሪያን(mobile app)፣ ራይድ ኦን ትሪፕ ፕላነር አፕ (Ride On trip planner app) በጉጉል ፕሌይ (Google Play) እና በአፕል አፕ (Apple app) ውስጥ እና በድረገጻችን ላይ ይገኛል።

ራይድ ኦን ኤክስትራ **(Ride On extRa)** ታዋቂ የሆነ አገልግሎት ሲሆን በሚጓዝበት መስመር ላይ ውስን የሆኑ ቦታዎች ላይ ብቻ የሚቆም ፍጥነት ያለው የትራንስፖርት ፕሮግራም አገልግሎት ነው። ይህ አገልግሎት ከራይድ ኦን (Ride On) በተለየ ሁኔታ ውስን የሆኑ ቦታዎች ላይ ብቻ የሚቆም ሲሆን፣ ተሽከርካሪዎች በሚበዙበት ጊዜ የጉዞ ጊዜን ይቀንሳል። የራይድ ኦን ኤክስትራ (Ride On extRa) አውቶብሶች ነጻ የዋይፋይ (WiFi) እና ቻርጅ ማድረጊያዎች ለተጨማሪ ምቾት ያቀርባሉ። ራይድ ኦን ኤክስትራ (Ride On extRa) መንገድ 101 ከMD 355 ከሌክ ፎረሰት (Lakeforest) ትራንዚት ማእከል ወደ ሜዲካል ሴንተር ሜትሮ ጣቢያ ከ 80 መቆሚያ ፈርማታዎች ይልቅ 13 ብቻ አሉት። የጉዞ መስመር (route) 101 ተሽከርካሪ የሚበዛበት ጊዜ ከሰኞ እስከ አርብ በ 20 ደቂቃ ውስጥ ይመላለሳል። በተጨማሪም፣ ሴፕቴምበር 2024 ላይ ስራ የጀመሩት አዳዲሶቹ ላይም (Lime) እና ፒንክ (Pink) የጉዞ መስመሮች የግሬት ሴኔካ ትራንዚት ኔትወርክ (Great Seneca Transit Network) አካል ሲሆኑ በሼዲ ግሮቭ (Shady Grove) የሜትሮ ጣቢያ ውስጥ ወደ አሉት ዩንቨርሲቲዎች የሚሄዱ ናቸው። የላይም (Lime) እና የፒንክ (Pink) የጉዞ መስመሮች ከራይድ ኦን (Ride On) 43፣ 63 እና 66 መንገዶች ተጨማሪ በመሆን አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ከሰኞ እስከ አርብ ተሽከርካሪ በሚበዛበት ጊዜ በየ 15 ደቂቃው እና ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ በየ 30 ደቂቃው ይነሳል። ወደፊት በሌሎች የካውንቲው ኮሪደሮች ላይ ኤክስትራ(extRa) የሚል ይፈልጉ።



# እንኳን በደህና መጡ

የትራንዚት አገልግሎት ዲፓርትመንት አስፈላጊ የሆነ ተልእኮን በመያዝ ለሞንቶጎመሪ ካውንቲ የመጓጓዣ አገልግሎት የሚያቀርብ ሲሆን ይህም ሰዎችን፣ ማህበረሰቦችን፣ የስራ ስፍራዎች፣ የትምህርት ተቋማትን፣ የመዝናኛ ስፍራዎችን እና ሌሎች ወሳኝ መዳረሻዎችን በማገናኘት ነው። ትራንዚት በተለይም ተሽከርካሪ በሚበዛባቸው ሰአቶች መንገድ ላይ ያሉ መኪናዎችን በመቀነስ የሞንቶጎመሪ ካውንቲን መሰረተ ልማት ውጤታማነትን ከፍ ያደርጋል። በተጨማሪም ትራንዚት በአካባቢው ኢኮኖሚ ላይ እና የመኖሪያ አካባቢዎችን ምቹ በማድረግ ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

# የአውቶብስ አጠቃቀም

### ለእርስዎ ምቾት እና ደህንነት:-

- አውቶብስ ሲሳፈሩ ክፍያዎትን ያዘጋጁ እና ክፍያውን እንዴት በትክክል ማስገባት እንዳለብዎ ይወቁ።
- ሌሎች በፍጥነት መሳፈር እንዲችሉ ወደ አውቶብሱ ኋለኛ ክፍል ይለፉ።
- አረጋውያን እና አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች ቅድሚያ ባላቸው መቀመጫዎች ላይ እንዲቀመጡ ያድርጉ።
- ሌሎች መቀመጥ ሲያስፈልጋቸው እባክዎትን ከአንድ በላይ ወንበር አይያዙ።
- የህጻናት መግፊያዎችን ከመተላለፊያዎች እና በሮች አካባቢ ያርቁ።
- አያጭሱ፣ አይመገቡ፣ አይጠጡ ወይም አይትፉ።
- የድምጽ መሳሪያዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የጆሮ ማዳመጫ ወይም ዝቅ ያለ የድምጽ መጠን ይጠቀሙ።
- በሚቆሙበት ጊዜ በአውቶቡሱ ላይ ካለው የደህንነት መስመር ጀርባ ይሁኑ (የፌዴራል ህግ)።
- አውቶቡሱ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ከኦፕሬተሩ ጋር ባለመነጋገር ኦፕሬተሩ አውቶቡሱን በአግባቡ እንዲነዳ ይፍቀዱለት።
- በጨዋነት፣ ከኋላ ውጡ እና ከኋላዎ ላለው ሰው እንዲወጣ የኋላውን በር በመክፈት ይያዙት።

# ተደራሽነት

ሁሉም አውቶብሶች ተደራሽ ናቸው። በአሜሪካ አካል ጉዳተኞች አዋጅ (Americans with Disabilities Act, ADA) እና የፌደራል ትራንዚት አስተዳደር መመሪያዎች መሰረት፣ ራይድ ኦን (Ride On) አንድ አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው የሚሰጠውን አገልግሎት ማግኘት እንዲችል እና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በሚችለው መጠን ሁሉንም ማድረግ የሚችለውን ጥረት ያደርጋል።

# የጉዞ እቅድ ማድረጊያ መረጃዎች

እነዚህ መረጃዎች ጉዞዎትን ከቤትዎ፣ ከስራ ቦታ ወይም መንገድ ላይ ሆነው ለማቀድ እንዲችሉ ያስችሉዎታል። እነዚህ አሰራሮች ቀጣይነተ ባለው መንገድ ማሻሻያ እየተደረገባቸው እንደሆነ እና ሁልጊዜም ምርጥ የሆነ የጉዞ ልምድ እንዲኖርዎት እንደሚያስችልዎት ይወቁ።

- ራይድ ኦን ትሪፕ ፕላነር (Ride On Trip Planner): ow.ly/IHEo50Rk8G6
- ራይድ ኦን ሪል ታይም (Ride On Real Time): rideon.app/busmap
- የጉግል ካርታ (Google Maps): www.google.com/maps/
- የሜትሮስ ትሪፕ ፕላነር (Metro's Trip Planner): www.wmata.com
- ለጉዞ እቅድ ድጋፍ MC311 የመረጃ ማእከልን ማግኘት ይችላሉ ይህም ሞንቶጎመሪ ካውንቲ ውስጥ 311 ብለው በመደወል ወይም ከካውንቲው ውጪ ከሆኑ 240-777-0311 ብለው መደወል ይችላሉ።

በረዶ፣ አውሎ ነፋስ ወይም ሌሎች ራይድ ኦን (Ride On) የተለመደ ሳምንታዊ መርሀግብሩን እንዳይከተል የሚያደርጉ ልዩ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ፣ የአውቶብስ አገልግሎት በ'S' የአገልግሎት እቅድ ሊሰራ ይችላል (ይህም በእንግሊዘኛ እና ስፓኒሽኛ ይገኛል )።

# የሲስተም ካርታ (System Map)

እባክዎትን www.RideOnBus.com – "Trip Planning" ገጽን በመጎብኘት የራይድ ኦን (Ride On)ን ኤሌክትሮኒክ ካርታ ማየት ይችላሉ። የራይድ ኦን (Ride On) መንገዶችን/መርሀግብሮችን ለማግኘት እባክዎትን "Ride On Schedules" ገጽን የሚከተለው ድህረ ገጽ ላይ ይመልከቱ። www.RideOnBus.com

# ስማርትሪፕ ካርድ (SmarTrip® Card)




ስማርትሪፕ (SmarTrip®)– በዋሺንግተን ዲሲ አካባቢ ላለው የሜትሮ እና ክልላዊ ትራንዚት አገልግሎት ለመጠቀም የሚያስችል መክፈያ መንገድ ነው።ስማርትሪፕ (SmarTrip®) ክልሉ ውስጥ በትራንዚን መሄድን ቀላል ያደርጋል እና ገንዘብዎትን ይቆጥብልዎታል። የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ተጠቃሚ ተጓዦች ይህን ተጠቅመው ለሜትሮሬል (Metrorail)፣ ለሜትሮ ባስ (Metrobus)፣ ለራይድ ኦን (Ride On) እና ሜትሮ ጣቢያዎቸን ላይ ለመኪና ማቆሚያ መክፈል ይችላሉ።

- **የፕላስቲክ ካርዶች፣** የስማርትሪፕ (SmarTrip) ካርድዎን በሜትሮ መግቢያ፣ የአውቶብስ ክፍያ መክፈያ ማሽኖች፣ የሜትሮ መኪና ማቆሚያ ላይ ባሉ ክብ የሆኑ ምልክቶች ላይ በማስነካት ይጠቀሙ። ለተጨማሪ መረጃ ይህን ድህረ ገጽ ይመልከቱ። https://www.wmata.com/fares/smartrip/faq.cfm
- **ሞባይል መክፈያ ፣** የሞባይል ስልክዎትን በሜትሮ የክፍያ በር ላይ፣ የአውቶብስ ክፍያ ማሽን ወይም የሜትሮ መኪና ማቆሚያ ጋራዦች ላይ በማስነካት ይክፈሉ። ለመረጃ ይህን ድህረ ገጽ ይመልከቱ። www.wmata.com/fares/mobilepay/

# ስማርትሪፕ ካርድ (SmarTrip® Card)

(የቀጠለ)

### ማስታወስ የሚገቡ ነጥቦች:-

- ስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ በተደጋጋሚ የሚሞላ ሲሆን እስከ $300 ድረስ ሊይዝ ይችላል።
- የተመረጡ የአውቶብስ እና የሜትሮ ማለፊያዎችን የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ በኦላይን መሙላት ይችላሉ። ካርዱ በአንድ ጊዜ እስከ ሁለት ማለፊያዎችን መያዝ ይችላል።
- ለደንበኞች አገልግሎት 1-888-SMARTRIP (762-7874) ብለው ይደውሉ ወይም በ smartrip@wmata.com ኢሜይል ያድርጉ። ለደንበኞች ድጋፍ አገልግሎት ካርዶች መመዝገብ አለባቸው።
- ደንበኞች አውቶብስ ውስጥ ወይም ሜትሮ ጣቢያዎች ያላቸውን ቀሪ ሂሳብ ማረጋገጥ እና ካርዳቸው ላይ ገንዘብ መሙላት ይችላሉ።
- ስማርትሪፕዎ (SmarTrip®) ከተሰረቀ ወይም ቢጠፋ ያለዎትን ቀሪ ሂሳብ መልሰው ማግኘት ይችላሉ። ያስታውሱ:- ይህንን እድል ለመጠቀም ካርዱ ቀድሞ መመዝገብ አለበት።

### በካርድዎ ውስጥ ገንዘብ ለመሙላት:-

- በሜትሮሬል (Metrorail) ውስጥ የሚገኙ የክፍያ ማሽኖችን ወይም የማለፍያ ማሽኖችን ወይም የአውቶብስ የመክፈያ ማሽኖችን በመጠቀም ወይም ተሳታፊ በሆኑ ሱቆች ውስጥ መሙላት ይችላሉ። (ቦታዎችን ለማወቅ ይህን ድህረ ገጽ ይመልከቱ wmata.com)

### ፌርካርድ (Farecard) ወይም ፓስ (Pass) ማሽንን በመጠቀም ገንዘብ እንዴት መጨመር ይቻላል

- በማሽኑ ላይ ካርድዎን በማስነካት መመሪያዎቹን ይከተሉ።
- ገንዘብ ወይም የፌር ካርድ (farecard) ያስገቡ (ዋጋው $20 ወይም ከዚያ በታች)። በተጨማሪም Visa፣ MasterCard፣ Discover፣ American Express፣ JCB ወይም ATM ካርድ ሊጠቀሙ ይችላሉ (እያንዳንዱ ግዢ ለየብቻው ሊካሄድ ይገባል።




- የሚያዩት አዲስ የገንዘብ መጠን ካርዱ ውስጥ እንዲኖር የሚፈልጉት ያህል እስከሚሆን ድረስ የመደመር (+) ወይም የመቀነስ (-) ምልክቶችን ይንኩ። በፌር ካርድ ( farecard) ካርድ ላይ የሚጨምሩ ከሆነ የተጨመረው የገንዘብ መጠን የፌር ካርድን (farecard) ለመተካት ከሚያስፈልገው ዋጋ ማነስ አይችልም።
- ካርዱን ለመጨረሻ ጊዜ ማሽኑ ላይ ያስነኩ። ይህም ካርዱ ላይ ለውጥ በማሳየት አዲሱን የገንዘብ መጠን ያሳያል። በተጨማሪም በፌርካርድ (Farecards) ላይ የ 1 ቀን የ 7 ቀን የሜትሮሬል (Metrorail) ማለፊያ በመጨመር ማሽኖቹን ማለፍ ይችላሉ።

### ክፍያዎትን በስማርት ትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ መክፈል:-

- በሜትሮሬል (Metrorail) የፌርጌት (faregate) ላይ እና የአውቶብስ ክፍያ ማሽን ላይ እና የሜትሮሬል (Metrorail) ጣቢያ መኪና ማቆሚያ ላይ በሚገኘው ስፍራ ላይ ካርድዎን ያስነኩ።
- ትክክለኛው መጠን ከስማርት ካርድ(SmartBenefits)፣ ከተቀመጠው ዋጋ ይቀነሳል ወይም የጉዞው ማለፊያ ይረጋገጣል።
- ወደ ሜትሮሬል(Metrorail) ሲስትም ለመግባት ተሽከርካሪ በማይበዛበት ጊዜ $2.00 እና ተሽከርካሪ በሚበዛበት ጊዜ $2.25 (ለአረጋውያን/አካል ጉዳተኞች ነጻ) ያስፈልጋል።

**ያስታውሱ:-**አካውንቶን በሚከተለው ድህረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ:- smartrip.com.

# ዝውውሮች

- ራይድ ኦን (Ride On) የወረቀት ትራንስፈሮችን መስጠት እና መቀበል አቁሟል ።
- ነጻ ትራንስፈሮችን ከአንዱ ወደ ሌላው አውቶብስ ለማድረግ ፣ ሜትሮባስን (Metrobus) ወይም ራይድ ኦንን (Ride On) ጨምሮ የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ መጠቀም አለብዎት።
- ከአንዱ ወደ ሌላው አውቶብስ ዝውውር ለማድረግ የጊዜው ገደብ 2 ሰአት ነው።
- የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ተጠቃሚዎች በባቡር ጉዟቸው ላይ ከራይድ ኦን (Ride On) ወደ ሜትሮሬል (Metrorail) ዝውውር ሲያደርጉ $1.00 ተቀናሽ ያገኛሉ።
- የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ተጠቃሚዎች ከሜትሮሬል (Metrorail) ባቡሮች ወደ ራይድኦን (Ride On) ዝውውር ሲያደርጉ ቅናሽ አያገኙም። ይህም ማለት ለSmarTrip® ተጠቃሚዎች የሚከፈለው የአውቶብስ ክፍያ ከአውቶብስ ክፍያ በኋላ $1.00 ነው።
- የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ጥቅሞች:- አውቶብስ እና ሜትሮሬል (Metrorail) ሲጠቀሙ በፍጥነት ለመሳፈር እና ቀላል የወጪ ክትትል ለማድረግ ያስችላል ብሎም $1.00 ቅናሽ ያገኛሉ

# ታይትል 6 (Title VI)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ማንም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በማንነት ምክንያት፣ በ 1964 የሲቪል መብቶች ህግ ታይትል 6 እና በ1987 የሲቪል መብቶች ህግ እንደተደነገገው ማንኛውም ግለሰብ ፣ አገልግሎት ከማገኘት እንደማይገለል፣ እንደማይከለከል እና በማንኛውም መንገድ መድሎ እንደማይፈጸምበት ያረጋግጣል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን የሚከተለውን ድህረ ገጽ ይመልከቱ ። http://www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/titlevi.html.

# ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች፣ ምስጋናዎች እና ቅሬታዎች

የኤምሲዲኦቲ (MCDOT) አገልግሎት ጥያቄ፣ ቅሬታ ወይም ምስጋና ለማቅረብ በ 311 ይደውሉ። ከካውንቲው ውጪ ሲደውሉ በ 240-777-0311 ይደውሉ ወይም በ MC311 ድረገጽ በኩል ያስገቡ፣ www.montgomerycountymd.gov/mc311 እባክዎ የአውቶብሱን መንገድ ቁጥር፣ ቀን፣ ሰአት፣ ስፍራ እና መዳረሻ ያቅርቡ።

የአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን (American with Disabilities, ADA) አስፈላጊ የራይድ ኦን አገልግሎት ለማግኘት የሚያስፈልግዎ ከሆነ MC311 240-777-0311 TTY 711፣ ወይም በሚከተለው ኢሜል ይጠቀሙ። RideOn.CustomerService@montgomerycountymd.gov.